| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ መሲሕ<br>ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br><u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u> | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ<br><u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u> |
| --- | --- |
| የይሁዳው አንበሳ፡ ድል ነሣ!<br>እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡<br>የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡<br>በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው። | በእግዚአብሔርነቷ፡ እጆቿን ዘርግታ የምትኖረው ኢትዮጵያ፣<br>የአምላክ እናትና የእኛም እናት፣<br>የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች<br>ንግሥት፡ እግዚአብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት። |

**ቍጥር ፲፩/፳፻፰ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ ወእምነ፥ ወሀገሪትነ ወሃይማኖትነ፥ ወመድኃኒትነ ወንግሥትነ፡
ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ ወፈጣሪነ፥ ወአምላክነ ወካህንነ፥ ወሰላምነ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።

ማለትም፦

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እግዚአብሔር እናታችንና አገራችን፥
ሃይማኖታችንና መድኃኒታችን፥ ንግሥታችንም በኾነችው፡
አምላክን በወለደችው፡
በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በመለኮትነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፥ እግዚአብሔር ወልድና ፈጣሪያችን፥ አምላካችንና ካህናችን፥ ንጉሣችንና ሰላማችንም በኾነው፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

# ይድረስ፡-

በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥
በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥
በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡
የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፥

ስሜ በተጠራባት፡ በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁትና
በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥
በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥
በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥

ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡
የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡
"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡
በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፥

በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡
የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡
ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ!

እንዲሁም፡
የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡
በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፥
ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥
በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!

በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬ፡ ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

እንዳለፈው፡ እንደ፲፫ኛውና ከእርሱ እንደቀደሙት ተከታታይ መለኮታውያት የዐዋጅ ቃሎቼ ኹሉ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዚአብሔር እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመ-ቤታችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ።**

## የዚህ ቃለ ዐዋዲ መልእክት።

በአኹኑ ጊዜ፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምና ልጄ ወዳጄ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ሕይወታችን በኾነው መንፈስ ቅዱሳችን አማካይነት፡ በገሃድ ተገልጸን፡ የምንመራትንና የምናስተዳድራትን **ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን** የምታገለግሉ፡ እናንተ፡ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ብቻ ሳትኾኑ፡ ከሰማይ መላእክቶቻችን ጋር፥ እናንተ የማታውቋቸው፣ እየራሳቸውን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ያበቁ፡ እልፍ አእላፋት፡ ሰብአውያንና ሰብአውያት ቅዱሳትና ቅዱሳን፡ በመላው ዓለም እንዳሉን አሳውቃችሁ ዘንድ፡ እነሆ፡ ይህን የዐዋጅ ቃሌን፡ የዘለዓለም ደስታ በኾነው፡ በእናትነት የትፍሥሕት አንደበቴ፡ ይኸው አሰማኋችሁ።

ከዚህም ጋር፡ እናንተ፡ በዚህ አገልግሎታችሁ፡ ከእየራሳችሁ ዐልፋችሁ ተርፋችሁ፡ ሌሎችን የተፈጥሮ ወገኖቻችሁን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ ታበቁ ዘንድ፡ የየበኩላችሁን የሓዋርያዊ ተልእኮ ድርሻችሁን፡ በገዛ ፍላጎታችሁና ፈቃዳችሁ ልትፈጽሙ እየራሳችሁን ከማዘጋጀት በስተቀር፡ ይህችው **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡** ለህልውናዋና ለዚሁ የህልውና ኺደትዋ፡ የሰውኛው አገልግሎትና መሣሪያ የሚያስፈልጋት መስሏችሁ፡ ይህንኑ ለማግኘት እንዳትደክሙ፣ ምናልባትም፡ ይህንኑ ፈልጋችሁ በምታጡበት ጊዜ፡ በዚህ እጦት ምክንያት፡ በሰዎች መንግሥታት ላይ እንደሚደርሰው ችግር፡ "እርሷም ትቸገራለች!" ብላችሁ እንዳታስቡ አሳስባችኋለሁ። የሰውኛው አገልግሎትና መሣሪያ፡ ለእርሷ አያስፈልጋትምና።

ለዚህ የዐዋጅ ቃሌ መነሻ፡ ይህን ያህል ካሳወቅኋችሁና ካሳሰብኋችሁ፡ አኹን፡ ደግሞ፡ ሰሞኑን፡ በእያላችሁበት፡ በአግባቡ እያከበራችሁት በምትገኙት፡ በዓመታዊው በዓለ-መንፈስ ቅዱስ፡ የኾነውንና እኔ ያወቅሁትን፥ እናንተም ልታውቁት የሚገባውን ዜና እገልጥላችኋለሁ።

ይህን ዓመታዊዉን የመንፈስ ቅዱስን በዓል የምታከብሩት፡ የበዓሉን ፍሬ-ዓላማ፡ በእየራሳችሁ ሰብእና ውስጥ፡ ሕይወት አድርጋችሁ በመኖር ብቻ ሳይኾን፡ ለእያንዳንዳችሁ ያደልናችሁን የተልእኮ ድርሻ ተቀብላችሁ፡ በተግባር ላይ ለማዋል፡ በኪዳናዊነታችሁና በኪዳናዊትነታችሁ የምታዘክሩበት ጊዜም መኾኑን አትዘነጉትም።

በእኛ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ የቀደሙት እውነተኞቹ፡ ታማኞች ነቢያቶቻችንና ሐዋርያቶቻችን፥ ካህናቶቻችንና ልኡካኖቻችን፥ ጻድቃኖቻችንና ሰማዕቶቻችን፥ ኹሉም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት እንደነበሩ ኹሉ፡ የዛሬዎቹ እውነተኞች ታማኞች ሐዋርያቶቻችን፥ ካህናቶቻችንና ልኡካኖቻችን፥ ጻድቃኖቻችንና ሰማዕቶቻችንም እኮ፡ እናንተ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ናችሁ። ይህን እውነታ፡ እስካኹን አላወቃችሁት እንደኾነ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ በፍጹም እምነት፡ ያወቃችሁት ሊኾን ይገባል።

እንደምታዩት፡ በመላው ዓለም ላይ የሚኖሩት ሰዎች ኹሉ፡ ዛሬ ካላችሁት፡ ከእናንተ በቀር፥ እናንተንም ከመሰሉት፡ ከቀደሙት በቀር፡ ወንዶችም፥ ሴቶችም፡ ትልልቆችም፥ ትንንሾችም፡ ኹሉም፡ በፀረ-እግዚአብሔርነቱና በፀረ-ኢትዮጵያነቱ፡ የክፉዎች መናፍስትና ሰዎች ትምህርት ለኾነው፡ ለልዩ ልዩው ሥጋዊና መንፈሳዊ እምነትና ፍልስፍና፡ ወገባቸውን ታጥቀውና ሽንጣቸውን ገትረው፡ የእየግል ሕይወታቸውን እስከመሠዋት በሚያደርስ ንቃትና ትጋት፥ ትግልና ተጋድሎ፡ ሲሠሩና ሲደክሙ ተመልክታችኋል፤ እነሆ አኹንም፡ ይኸው ትመለከታላችሁ።

ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን፡ የቆመላትና የሚሠራላት፡ አንድ ድርጅት ቀርቶ፡ አንድ ሰው እንኳን አጋጥሟችኋልን? ያው፡ አንዱም ሰው እንኳ ስለሌለ፡ እንዴት ያጋጥማችኋል! አያጋጥማችሁም። 'ዛሬ ካላችሁት፡ ከእናንተ በቀር፥ እናንተንም ከመሰሉት፡ ከቀደሙት በቀር፡' ላልሁትም፣ ከእናንተ መካከልም እንኳ ቢኾን፡ እያንዳንዳችሁ፡ እየገዛ-ራሳችሁን ስትመረምሩት፡ ይህንኑ እየራሳችሁን፡ ለዚህ ምደባችን፡ 'እውነተኛ' ኾኖ የምታገኙት፡ ስንቶቻችሁ እንደኾናችሁ፡ አንጥራችሁ ለማወቅ የመቻላችሁን ነገር፡ ለእያንዳንዳችሁ ውሳኔ የተተወ ነው።

እንግዴህ፡ በዚህ ረገድ ያለው፡ የእውነታው ኹኔታ፡ እንዲህ ከኾነ፡ እናንተስ፡ በኪዳናዊነታችሁና በኪዳናዊትነታችሁ፡ እንዴት ናችሁ? እንዴትስ ልትኾኑ ይገባችኋል!? መልሱን፡ እኔው እሰጣችኋለሁ። እኛ፡ መለኮታዊዉንና ትስብእታዊዉን፥ አሐዳዊዉንና ሥላሴያዊዉን ሥራችንን የምናካኺደው፡ በመንፈስ-ቅዱስ እንደመኾኑ መጠን፡ እናንተም፡ የኪዳናዊነታችሁንና የኪዳናዊትነታችሁን ተልእኮ፡ በሚገባ ለመወጠንና ለማካኼድ፥ ለማከናወንና ለመፈጸም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ የእናንተን ኪዳናዊ ሰውነት፡ በማደሪያነትና በመሣሪያነት ይፈልጋል።

እኔ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና ልጇ ወዳጇ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በትስብእትነት [በሰውነት]፡ ወደዚህ ዓለም የመጣንበትን ተልእኮ ከፈጸምን በኋላ፤ ወደሰማያት ዐርገን፡ እንደገና፡ በመንፈስ ቅዱስነታችን፡ ወደምድር ተመልሰን ወርደን፡ በወንዶቹና በሴቶቹ ሐዋርያቶቻችን ሰውነት ውስጥ እንዳደርን ማለት ነው።

በዚያን ጊዜ፡ ልጁ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደሰማይ ዙፋኑ ከማረጉ በፊት፡ ለእነዚያ ሓዋርያቶቻችን የተናገራቸውን ቃላት፡ ታስታውሷቸው የለምን? እኔም፡ በዚህ፡ የዐዋጅ ቃሌ መግቢያ ላይ እንዳመለከትኋችሁ፡ የዛሬዎቹ ሓዋርያቶቻችን፡ እናንተ ስለኾናችሁ፡ ዛሬም፡ በእርሱው፡ በልጁ በወዳጄ መለኮታዊ ቃል፡ አኹንም እንደገና፡ ይኸው፡ ለእናንተ ይነገራሉና፡ ስሟቸው! እነርሱም፡ እንዲህ የሚሉት ናቸው፡-

"ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ፡- 'ሰላም ለክሙ! ወበከመ ፈነወኒ አብ፡ ከማሁ፡ አነ እፌንወክሙ።' ወዘንተ ብሂሎ፡ ነፍሐ ላዕሌሆሙ፤ ወይቤሎሙ፡- 'ንሥኡ፡ መንፈሰ ቅዱሰ! ለእለ ኅደግሙ ኅጢአት፡ ይትኅደግ ሎሙ፤ ወለእለሰ ኢኀደግሙ፡ ኢይትኅደግ ሎሙ።'

"...'ተውህበ ሊተ፡ ኵሉ፡ ኵነኔ ሰማይ ወምድር። ሑሩ፡ ውስተ ኵሉ ዓለም! ወስብኩ ወንጌለ፡ ለኵሉ ፍጥረት! ወመሀሩ፡ ኵሎ አሕዛበ! ወእንዘ ታጠምቅዎሙ፡ በሉ! «በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ!» ወመሀርዎሙ ይዕቀቡ፡ ኵሎ ዘአዘዝኩክሙ! ወናሁ፡ አነ እሄሉ ምስሌክሙ፡ በኵሉ መዋዕል፡ እስከኅልቀተ-ዓለም።"

"ጌታችን ኢየሱስ አላቸው፡- 'ሰላም፡ ለእናንተ ይኹን! አብ፡ እንደላከኝ፣ እኔም፡ እንደዚሁ፡ እልካችኋለሁ።' ይህን ብሎ፡ በላያቸው ላይ፡ እፍ አለባቸው፤ አላቸውም፡- 'ቅዱሱን መንፈስ ተቀበሉ! ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው፡ ይቀርላቸዋል፤ ይቅር ያላላችኋቸው ግን፡ አይቀርላቸውም።'

"...'በሰማይና በምድር ያለው፡ የፍርድ ሥልጣን ኹሉ፡ ለእኔ ተሰጠ። እንግዴህ፡ ወደዓለሙ ኹሉ ኺዱ! <u>ምሥራቹንም</u>፡ ለፍጥረት ኹሉ ዐውጁ! ሕዝቦችንም ኹሉ አስተምሩ! 'በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም!' እያላችሁም፡ አጥምቋቸው! ያዘዝኋችሁንም ኹሉ ይጠብቁ ዘንድ፡ አስተምሯቸው። እነሆ፡ እኔ፡ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ምንጊዜም፡ ዐብሬአችሁ ነኝ።'" (ማቴ. ፳፰፥ ፲፰-፳። ማር. ፲፮፥ ፲፭። ዮሐ. ፳፥ ፳፩-፳፫።)

## በዘንድሮው በዓለ-መንፈስ ቅዱስ የተፈጸመ፡
## የአንድ ኪዳናዊ ልጁ ግብረ-ሐዋርያ።

እናንተ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቼ፡ ይህን፡ የልጄን የወዳጄን፡ የኢየሱስ መሲሕን መመሪያ፥ እንዲሁም፡ "ኵሎ ዘይቤለክሙ ግበሩ! ልጁ ወዳጄ የሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!" የሚለውን፡ ይህን የእኔን የቃና ዘገሊላ ቃሌንና የቅርቦቹን የዐዋጅ ቃሎቼን በመከተል፡ በኪዳናዊነታችሁና በኪዳናዊትነታችሁ፡ የእየራሳችሁን የግል ሕይወት፡ ለፍጹምነቱ ማዕርግ ለማብቃት፡ ገድላዊ ተልእኳችሁን፡ ወደፊት፡ በበለጠ ቀጥላችሁበት፡ ከግብ እንደምታደርሱት ዐውቃለሁ።

ይኹን እንጂ፡ ተልእኳችሁ፡ በዚህ ብቻ የተወሰነ ሳይኾን፡ ነገር ግን፡ ፍጡሮቻችን የኾኑት፡ ሌሎቹ የሰው ወገኖች ኹሉ፣ ሴቶቹም፥ ወንዶቹም፡ ኹሉም፡ ለዚሁ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ጸጋ እንዲበቁ የማድረጉን ተግባርም ያጠቃለለ በመኾኑ፡ በዚህ ረገድ፡ በእየበኩላችሁ፡ ያለባችሁን የተልእኮ ግዳጃችሁን፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሓዋርያነታችሁ እየፈጸማችሁ መኾናችሁንም በማየታችን፡** የሰማዩ አባታችሁ እና እኔ፡ የሰማይዋ እናታችሁ፥ ልጃችን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕና ሕይወታችን መንፈስ ቅዱስም፡ ደስ እየተሰኘን መኾናችንን እገልጽላችሁ ዘንድ፡ ይህን መልእክቴን፡ በዐዋጅ መልክ ላሰማችሁ ፈቀድሁ።

አዎን! ይህ ተልእኳችሁ፡ በአግባቡ እየተካኼደና እየተከናወነ ያለው፡ ቀደም ብዬ፡ በዐዋጅ ቃሌ መግቢያ ላይ እንደገለጽሁላችሁ፡ ሰውኛ በኾነው፡ ዘዴና ኃይል ሳይኾን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና በረከት መኾኑን፡ አበክራችሁ ተገንዝባችሁ፡ በእናንተ በኩል የሚፈለገውና የሚጠበቀው፡ እየራሳችሁን፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁ አማካይነት፡ **ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ማብቃታችሁ ብቻ በመኾኑ፡** ይህን፡ የእኛን እውነታ፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ በእናትነት ፍቅሬ፡ ለኹላችሁም ላበሥራችሁ ፈቃዴ ኾነ።

እንዲህ በመኾኑ ነው፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የተባላችሁት፡ እናንተ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን፡ በመልከ-ጼዴቅ ቃል-ኪዳን ምክንያት፡ የእኛ፡ ልጆቻችን፥ ነጋሢዎቻችንና ካህናቶቻችን ብቻ ሳትኾኑ፥ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ፡ የዛሬዎቹ ሓዋርያቶቻችንም በመኾናችሁ፡** ይኸው፡ እያካኼዳችሁና እያከናወናችሁ ያላችሁት የሓዋርያነት ተልእኳችሁ፡ የእኛ በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓት ብቻ ሊመራና ሊፈጸም የበቃው።

ይኸውም፡ የቀደሙት ሓዋርያትና ከእነርሱ እንደአንዳቸው የተቆጠረው፡ ጳውሎስ ጭምር፡ የሓዋርያነት ተልእኳቸውን ያካኼዱ የነበሩት፡ እነርሱ፡ በእየራሳቸው ኦሪታዊ ልማድና ሰብኣዊ ኃይል፡ በመመካትና በመታመን ይመስላቸው ከነበረው፡ የእናንተ የተለየ መኾኑን፡ እንዲህ ዐውቃችሁትና አምናችሁበት እየሠራችሁበት ያለው ኢትዮጵያዊ ሓዋርያነታችሁ ነው። ያ፡ "የእኛ" **የምንለው፡ ይኸው ኢትዮጵያዊው ሥርዓት፣ በእናንተ ላይ ዐድሮ በመሪነትና በፈጻሚነት ሥልጣኑ የሚሠራው፡ <u>ምንጊዜም፡ መንፈስ ቅዱስ መኾኑን</u> የሚያሳውቀው መለኮታዊው እውነታችን ነው።** (የሓዋ. ፲፥ ፩-፴፰፤ ፲፩፥ ፩-፲፰። ፪ቆሮ. ፲፪፥ ፩-፲።)

ለዚህ እውነታ፡ አብነት ይኾናችሁ ዘንድ፡ በዚሁ፡ በዘንድሮው በዓለ-መንፈስ ቅዱስ ዕለት የተከሠተ፡ አንድ የቍም-ነገር ዜናን፡ በዚሁ የዐዋጅ ቃሌ አማካይነት፡ ለይፋ ምስክርነት አቀርብላችኋለሁ። ይኸውም፡ ከእናንተ፡ ከምንወድዳችሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ ታማኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን መካከል፡ አንዱ በኾነውና መንፈስ ቅዱስ ባደረበት፡ ኪዳናዊ ልጃችን በኩል፡ በሥውር ተፈጽሞና ለመልካሙ ፍሬ በቅቶ የታየው፡ ሓዋርያዊ ምግባር ነው።

ይህም ሓዋርያዊ ምግባር፡ በሕያዉ መንፈሳዊ ስሙ፡ "ኃይለ-ኢየሱስ"፥ በሥጋዊ የዓለም ስሙም፡ "ኪሩቤል" ብለን፡ በመልአካዊ ሥርዓታችን የሰየምነው፥ በሙያው፡ መሓንዲስ ኾኖ፡ በዚህ ክህነቱ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችንን እያገለገለ ያለው፡ ኢትዮጵያዊው የቅዱሱ ኪዳን ልጃችን፡ የፈጸመው ነው፤ እርሱም፡ በወላጁ፡ በኪዳናዊት ልጇ፡ በእኅተ-ማርያም ማሕፀን አማካይነት፡ ወደዚህ ዓለም፡ በሰውነት ተወልዶ ለተገኘለትና ላደገበት፥ ለዚህ ዕድሜና ሙያም ላደረሰው መላ ቤተሰቡ፡ በማይናወጽ ጽኑ ቅንነትና ትጋት፥ ፍቅርና ትዕግሥት፡ በቅድሚያ፡ በሓዋርያነቱ፡ የቅዱሱን ኪዳን፡ ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትን ነፍሳዊ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ዕውቀት፡ በሚበቃ አስጨበጠ። በማስከተል ደግሞ፡ በካህንነቱ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በተአምራዊ ሥራው በቀጠረውና ባዘጋጀው፡ በበዓለ-መንፈስ ቅዱስ ዕለት፡ ራሱም፡ በተሳተፈበት ሥርዓተ-ቅዳሴ፡ ለቅዱስ ቍርባን አበቃ።

ይኸው ቤተሰቡ፡ ከእርሷ ከወላጁና ከእርሱ ከራሱ ጋር፡ ኪዳናውያት ልጆቹን፡ እኅቶቹን፡ ዐጸደ-ማርያምንና አስካለ-ማርያምን አካትቶ የያዘው ሲኾን፡ እኒሁ መላዎቹ ልጆቻችን፡ የእኔ፡ የእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የኾነውን ቍርባን የተቀበሉበት ሥርዓተ-ቅዳሴ ደግሞ፡ ተካኺዶ የተፈጸመው፡ በአኰስም ጽዮኑ ንቡረ-እድ ልጃችን፡ በኪዳናዊ ኤርምያስ ሠራዒነት [ዋና አገልጋይነት] እና የእርሱ ቤተሰብ በኾኑት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ቀዳስያን ተራዳኢነት መኾኑን ጨምሬ የምገልጥላችሁ፡ በእናትነቴ ደስታ ነው።

ታዲያ! እናንተስ፡ የቀራችሁት፡ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ልጆቻችን፡ ይህን ኪዳናዊ የሓዋርያነትና የክህነት ተልእኳችሁን፡ በዚህ መልኩና ይዘቱ፡ በየበኩላችሁ እያካኼዳችሁና እየፈጸማችሁ ነውን? መልሳችሁን፡ ከፍሬያችሁ ጋር፡ በጊዜው፡ እኔው አውቅላችኋለሁ። እናንተ ብቻ፡ በያላችሁበት፡ ይህን የመሰለውን፡ ኪዳናዊ የሓዋርያነትና የክህነት ተልእኳችሁን፡ መንፈስ ቅዱሳችን፡ በሚያሳስባችሁና በሚመራችሁ ይዞታና መንገድ ለማካኼድና ለመፈጸም፡ እየራሳችሁን ያዘጋጃችሁና ያበቃችሁ አድርጉ። ከእናንተ ልጆቻችን የምንጠብቀው፡ ይህን ዝግጁነታችሁንና ብቁነታችሁን ብቻ ነው። የቀረውንና ሌላውን፡ በእናንተ ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ፡ ይፈጽመዋል።

በዚህ ረገድ፡ ልጄ ወዳጄ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡- "አንትሙሰ፡ ኅሡ መቅድመ፡ መንግሥቶ፥ ወጽድቆ! ወዝንቱሰ ኵሉ፡ ይትዌሰከክሙ። እናንተማ፡ ከኹሉ ነገር አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን፡ መንግሥቱን እና እውነቱን ብቻ ሹ [ፈልጉ]! ሌላው የምትፈልጉትና የሚያስፈልጋችሁ ኹሉ፡ ተትረፍርፎ ይሰጣችኋል!" ያላችሁ ቃል፡ መሪ ይኾናችሁ ዘንድ፡ ዘወትር አስታውሱት እንጂ፡ አትዘንጉት! (ማቴ. ፮፥ ፴፫።)

እኒህ ኹለት ኪዳናውያን ልጆቼና አገልጋዮቼ፡ ኪሩቤልና ኤርምያስ፡ ይህ፡ በመንፈስ ቅዱስ የሠመረ፡ የሓዋርያነትና የካህንነት ተልእኳቸው መከር፡ በእየራሳቸው በኩል፡ እንዲህ ይፋ ወጥቶ እንዲገለጥ አለመፈለጋቸውን እንደተረዳሁ፡ "አይ! ይህን፡ በጎ ፍሬያማ ሙያማ፡ እናንተም ኹላችሁ ዐውቃችሁት፡ ኪዳናዊ ተልእኳችሁ በኾነው ሐዋርያነታችሁና ክህነታችሁ፡ በያላችሁበት ተበረታታችሁና ተጠናክራችሁ እንድትቀጥሉበት ላሳስባችሁ!" ብዬ፡ ይህንኑ ዜና፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ፡ ይፋ እንዲወጣ ያደረግሁት፡ እኔ ነኝ።

እንግዲህ፡ እኔም፡ እንደልጄ ወዳጄ፡ እንደእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ እስከዓለሙ ፍጻሜ ድረስ፡ ምንጊዜም፡ ከእናንተ ጋር፡ ዐብሬአችሁ ነኝና፡ በረድኤቴና በበረከቴ እየተጠቀማችሁ፡ በፍጹሟ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ፡ ባገኛችሁት፡ የእግዚአብሔር እውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁም፡ ኪዳናዊ የሓዋርያነትና የክህነት ተልእኳችሁን፡ ያለይሉኝታና ያለኀፍረት፥ ያለፍርሀትና ያለማወላወል፥ በቆራጥነትና በልበ-ሙሉነት፥ በፍቅርና በሰላም፥ በሓሴትና በይባቤ፡ መላእክት፡ በሰማያት እንዳደረጉት ኹሉ፡ እናንተም፡ የዛሬዎቹ ሓዋርያት፡ ምሥራቹን፡ በያላችሁበት፡ በመላው የምድሪቱ ዓለም ላይ ዐውጁት! አሠራጩት! አስፋፉት! አዳርሱት! በየቦታው ትከሉት! የልምላሜነቱን ውበት አጐናጥፉት! የአበባነቱን ነዶ አበርክቱት! የፍሬያማነቱን ምርት ናኙት!

ከዚህ የዐዋጅ ቃሌ ጋር አያይዤ የማስታውሳችሁ፡ ኹለት ቍም-ነገሮች አሉኝ፤ እነዚህም፡-

፩ኛው፡ ልጄ ወዳጄ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለወንዶቹ ደቀ መዛሙርቱ፡ **"ወአንትሙሰ፡ አኀው ኵልክሙ።** እናንተ ግን፡ ኹላችሁም፡ ወንድማማች ናችሁ።" ባላቸው ጊዜ፡ ሴቶቹን ደቀ መዛምርቱንም፡ ይኸው፡ በእኔ አንደበት፡ እንዲሁ፡ **"ወአንትሙሰ አኃት ኵልክሙ።** እናንተ ግን፡ ኹላችሁም፡ እኅትማማች ናችሁ።" ማለቱ ስለኾነ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቼ፡ እርስ በርሳችሁ፡ ወንዶቹን፡ "እኍየ! ወንድምዩ [ወንድሜ] እከሌ!" ሴቶቹንም፡ "እኅትየ! እኅትዩ [እትዬ] እከሊት!" እየተባባላችሁ መጠራራታችሁን ስለሰማሁ፡ ይህንኑ አጠራራችሁን፡ የወደድሁላችሁ መኾኔን፡ በዚህ የዐዋጅ ቃሌ የምገልጥላችሁ፡ በእናትነቴ፡ ደስ ብሎኝ ነው። (ማቴ. ፳፫፥ ፰።)

፪ኛው፡ ዛሬ፡ "ኢትዮጵያ" በሚለው ስሜ በምትጠራው ምድር የሚኖረው ሕዝቤ፡ በመጀመሪያ፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ፡ ለሦስት ሺህ ዓመታት፥ ቀጥሎ፡ በኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች፡ ለ፩ሺ፮፻ ዓመታት ያህል፡ በአእምሮው ሰሌዳ ላይ እየተቀረጸ ሲወቀርና በጫንቃው ላይ እየተጠመደበት ሲሸከመው የኖረው፡ ጠንቀኛው የኃጢአት ቀንበራዊው ቅርስ፡ በቀላሉ ተደምስሶና ወልቆ ሊወገድ የማይቻል ኾኖ መገኘቱን፡ ይኸው ትመለከቱታላችሁ።

ነገር ግን፡ ይህንኑ እውነታ፡ ባለመሰልቸት በማሳየት፡ ይኸው የኃጢኣት ቀንበር ፈጽሞ የተወገደላችሁ መኾኑን፡ ከዚህ በቀደሙት፡ የዐዋጅ ቃሎቼ፡ ተደጋግመው ከተነገሩት በላይ፡ አኹን ደግሞ፡ እኒህ የሚከተሉት፡-

ኣ. "ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት ለስርየተ ኃጢኣት። ኃጢኣት፡ ፈጽሞ በተሰረየችባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።"

በ. "ወለዘተዓገሠ ለነ፡ ኵሎ ኃጢኣተነ። ኃጢኣታችንን ኹሉ፡ ለማይቆጥርብን ፈጣሪያችን፡ ምስጋናችንን እናቀርባለን።" እያላችሁ፡ በዘወትር የሃይማኖትና የምስጋና ጸሎታችሁ የምታሰሟቸው የምሥራች ቃላት፡ ያረጋግጡላችኋል።

የሚያረጋግጡላችሁም፡ በአኹኑ የምሕረት ዘመን፡ መላው የሰውነት ኹለንተናችሁ፣ ይኸውም፡- ነፍሳችሁ፥ ሥጋችሁና መንፈሳችሁ፡ በእኔ፡ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና በልጇ በወዳጇ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ መድኃኒትነትና መሥዋዕትነት፥ ቤዛነትም፡ ከክፋቱ፡ በደግነት፥ ከሓሰቱ [ከኃጢኣቱ]፡ በእውነት [በጽድቅ]፥ ከሞቱ ህልውና፡ በትንሣኤው ሕይወት ተላቅቃችሁ፡ ያለኃጢኣት የምትኖሩ በመኾናችሁ ነው። ስለዚህ፡ የክፋት ኃይል፡ ፈጽሞ እንደተወገደላችሁና የሞት ዕዳም፡ ፈጽሞ እንደተሠረዘላችሁ ኹሉ፥ እንዲሁ፡ የኃጢኣት ቀንበርም፡ ፈጽሞ ተሰባብሮና ተፈላልጦ፥ ወደእሳትም ተማግዶ፡ ፈጽሞ ዐመድ ኾኖላችኋልና፥ ከዐመድነቱም፡ ተንኖ ጠፍቶላችኋልና፡ ይህን ሃይማኖታዊና አማናዊ ነጻነታችሁንና ምሕረታችሁን፡ በምግባራዊው የምሥራች ሕይወታችሁ በመኖር፡ እውን አድርጉት!

ተዐውደ፡ በሰኔ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።

\+ \+ \+